የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 13
ADDIS ABABA 31st December 2012

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸፰/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................ገጽ ፮ሺ፯፻፲

CONTENTS

Regulation No. 278/2012

Vital Events Registration Agency Establishment Council of Ministers Regulation…………..…..… Page 6710

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፰/፪ሺ፭

## የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ እንዲሁም በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ አንቀጽ ፬ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፰/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 278/2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE VITAL EVENTS REGISTRATION AGENCY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 4 of the Registration of Vital Events and National Identity Card Proclamation No.760/2012.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Vital Events Registration Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 278 /2012 ''.

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Registration of Vital Events and National Identity Card Proclamation No. 760/2012;

2/ definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

3/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Justice, respectively;

ያንዱ ዋጋ
Unit price 3.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

፫. **መቋቋም**

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪/ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **የኤጀንሲው ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባራትን በአገር አቀፍ ደረጃ የመምራት፣ የማስተባበርና የመደገፍ፤ እና

፪/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃዎችን በማዕከል አደራጅቶ የመያዝ፡፡

፮. **የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በአዋጁ መሠረት ወሳኝ ኩነት በአግባቡ መመዝገቡንና ምስክር ወረቀት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

፪/ ለክልሎች የሚያገለግሉ የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ሥርጭትን በሚመለከት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር ይተባበራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫/ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖሩ ዜጎችንና በግዳጅ ላይ ያሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላትን የሚመለከቱ እንዲሁም በኢትዮጵያ መርከቦች ላይ የሚከሰቱ ወሳኝ ኩነቶችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የክብር መዝገቦችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፤

፬/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የድርጊት መርሀ ግብር እና የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓትን ከክልሎች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፭/ የወሣኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነትን አስመልክቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርትና ሥልጠናዎች ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፮/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የጥራትና የሽፋን ደረጃ ለመገምገምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ በምዝገባ ሂደት በታዩ የአሠራር ችግሮች ላይ የመፍትሔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፯/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተስማሚ በሆነ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚሠራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

4/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Establishment**

1/ The Vital Events Registration Agency (hereinafter the "Agency") is hereby established as an autonomous federal organ having its own legal personality.

2/ The Agency shall be accountable to the Ministry.

4. **Head Office**

The Agency shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere as deemed necessary.

5. **Objectives**

The Agency shall have the objectives:

1/ to direct, coordinate and support the registration of vital events at national level; and

2/ to centrally organize and keep records of vital events.

6. **Powers and Duties of the Agency**

The Agency shall have the powers and duties to:

1/ ensure the proper registration of vital events and the issuance of certificate of registration in accordance with the Proclamation;

2/ collaborate with and provide assistance to the appropriate regional organs in the preparation and distribution of registers of civil status to be used by the regions;

3/ prepare and distribute registers of civil status to be used for the registration of vital events involving Ethiopians residing in foreign countries and defense force members on active duty and vital events occurring on Ethiopian ships;

4/ in cooperation with the regions, prepare action plans for registration of vital events and a system for the usage of information, and monitor the implementation of same;

5/ provide or cause the provision of awareness creation education and trainings, through different methods, on the importance of registration of vital events;

6/ conduct surveys on the quality and coverage of vital events registration, and forward recommendations to resolve problems encountered in the course of the registration;

7/ facilitate the application of vital events registration and information exchange system which is supported by user friendly technology;

፰/ በአዋጁ መሠረት የተሰበሰቡ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲተላለፉ አስፈላጊውን የማስተባበር ሥራ ያከናውናል፤

፱/ ለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል ያደራጃል፤ የሚዘረጋው ቴክኖሎጂና የሚሰበሰበው መረጃ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋል፤

፲/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩/ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

፲፪/ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሀገሪቱ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የተሟላ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፤

፲፫/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤ እና

፲፬/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል::

## ፯. የኤጀንሲው አቋም

ኤጀንሲው፡-

፩/ የወሳኝ ኩነት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፫/ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፬/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል::

## ፰. የምክር ቤቱ አባላት

፩/ የምክር ቤቱ አባላት አግባብ ካላቸው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የክልል አካላት ተውጣጥተው በመንግሥት ይሰየማሉ::

፪/ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ይሆናል::

፫/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ ፀሐፊ ይሆናል::

## ፱. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በተመለከተ የፖሊሲ ሃሣብ ያመነጫል፤

8/ undertake coordination activities necessary for the timely transmission of collected data to the relevant organs as stipulated by the Proclamation;

9/ organize central data base for registered vital events, and take necessary precautionary measures to protect the technology infrastructure and the data thereof from risk exposure;

10/ forward policy ideas on vital events registration system to the relevant organ, and implement same upon approval;

11/ act in collaboration with the relevant federal and regional state organs;

12/ coordinate government organizations, societies and charity organizations to provide the necessary support in the making of the country's vital events registration system comprehensive;

13/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name; and

14/ perform such other related activities as may be required for the attainment of its objectives.

## 7. Organization of the Agency

The Agency shall have:

1/ a Vital Events Council (hereinafter the "Council");

2/ a Board of Management (hereinafter the "Board");

3/ a Director General and, as necessary, a Deputy Director General to be appointed by the government; and

4/ the necessary staff.

## 8. Members of the Council

1/ Members of the Council shall be drawn from the relevant federal government offices and regions and be designated by the government.

2/ The Minister shall be the Chairperson of the Council.

3/ The Director General of the Agency shall be the secretary of the Council.

## 9. Powers and Duties of the Council

The Council shall have the powers and duties to:

1/ initiate policy ideas regarding vital events registration;

፪/ ሀገር አቀፍ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የድርጊት መርሀ ግብርን ይገመግማል፤ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፤

፫/ የኤጀንሲውን እና የክልል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ አካላትን የክንውን ሪፖርቶች ይገመግማል፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

፬/ አዋጁ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መደረጉን ይገመግማል፤ ሳጋጠሙ የአፈጻጸም ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፤

፭/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

፲. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ-ጉባዔ ይሆናል።

፫/ ምክር ቤቱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፲፩. <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፪/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

፲፪. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤

፪/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ይገመግማል፤

፫/ በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን ይገመግማል፣ ያፀድቃል፤

፬/ የአዋጁን አፈጻፀም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ እንደ አግባቡ ይወስናል፤

፭/ ከኤጀንሲው ሥራዎች ጋር በተገናኘ የሚመለከታቸው አካላትን ያስተባብራል።

2/ review the country's vital events registration action plans, and forward recommendations for improvements;

3/ review performance reports of the Agency and regional vital events registration organs, and forward recommendations for improvements;

4/ review the nationwide implementation of the Proclamation, and suggest recommendations for implementation problems;

5/ establish sub-committees as may be necessary.

10. <u>**Meetings of the Council**</u>

1/ The Council shall meet twice a year; provided, however, that it may hold a meeting at any time where necessary.

2/ The presence of more than half of the members of the Council shall constitute a quorum.

3/ Decisions of the Council shall be passed by majority vote; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

11. <u>**Members of the Board**</u>

1/ Members of the Board, including the Chairperson, shall be designated by the government, and their numbers shall be determined as necessary.

2/ The Director General of the Agency shall be member and secretary of the Board.

12. <u>**Powers and Duties of the Board**</u>

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee the activities of the Agency;

2/ review the annual work program, budget and performance reports of the Agency;

3/ review and approve guidelines to be issued by the Agency;

4/ deliberate and, as may be appropriate, decide on issues related with implementation of the Proclamation;

5/ coordinate relevant organs in relation with activities of the Agency.

## ፲፫. የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ ቦርዱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፬. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋ ጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነ ቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 13. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet once a month; provided, however, that it may hold a meeting at any time where necessary.

2/ The presence of more than half of the members of the Board shall constitute a quorum.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of tie.

4/ Without prejudice to the provision of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

## 14. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and, subject to the general direction of the Ministry, direct, administer and control the activities of the Agency.

2/ Without prejudice to the generality stated in sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Agency specified in Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Agency in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plans, annual plans and budgets of the Agency and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and operational program of the Agency;

e) represent the Agency in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the operational and financial reports of the Agency.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

**፲፭. በጀት**

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

**፲፮. የሒሳብ መዛግብት**

፩/ ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ።

**፲፯. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**15. Budget**

The Agency's budget shall be allocated by the government.

**16. Books of Accounts**

1/ The Agency shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

**17. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 31st day of December, 2012.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ